# ማርቆስ 1:14-15
# የእግዚአብሔር ወንጌል !

አዘጋጅ ፡- ተካልኝ ኃ/ሚካኤል

ወንጌል በክርስትና ውስጥ ትልቁን ስፍራ የያዘ ነገር ሳይሆን ክርስትና ነው ። ክርስትናን ለመረዳት ከተፈለገ የሚሰበከውን ወንጌል በጥንቃቄ መረዳት ነው ። በዚህ ወንጌል ላይ ቤተክርስቲያን ትቆማለች ። ቤተክርስቲያን የሚሻሻል እና የሚቀየር ወንጌል የላትም ። የዘለአለሙን ወንጌል እየሰበከች ለዘለአለም ትኖራለች ። ርዕሱ አይቀየርም ነገርግን ርዕሱ በእየለቱ በጥልቀት ይብራራል ። እንገታችንን ከወንጌል ዞር እናደርግም ምክንያቱም ወንጌሉ መልዕክት ረክተናል ።

ይህ ወንጌል ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ስለ ክርስቶስን ማንነት እና ስለ ክርስቶስ ስራ ብቻ ያነሳል። የጠፋውን ሊፈልግ ከሰማይ የመጣው እርሱ ነው ፣ ሕጉን በትክክል የታዘዘው እርሱ ነው ፣ የተሰቀለው እርሱ ነው ፣ ከሙታን የተነሳው እርሱ ነው ። እኛ አመስጋኞች ነን። እኛ ለማኞች ነን እርሱም በጎ አድራጊ ነው። እኛ ለምጻሞች ነን እርሱም ፈዋሽ ነው። እኛ ረባሾች ነን እርሱ ሰላም ነው።

ወንጌል የሚነግረን እኛ ለእግዚአብሔር ማድረግ ያለብንን ሳይሆን እግዚአብሔር ለእኛ ያደረገውን ነው ። እውነተኛው ወንጌል እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን የሚያድንበት የምሥራች ነው። ሰው በተፈጥሮው ኃጢያተኛ ነው እናም ይህንን ሁኔታ ለማስተካከል ምንም ተሰፋ የለውም። ነገር ግን እግዚአብሔር በኃይሉ በአዳኙ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት፣ መቀበር እና ትንሳኤ ሰውን ለመቤዠት መንገድን አዘጋጀ።

ሰው በኤደን ገነት በመውደቁ ምክንያት የሰው ልጅ "አእምሮው፣ ፈቃዱ፣ ሰሜቱ እና ስጋው" በኃጢአት ተበላሽተዋል። ሰው ከኃጢአተኛው ተፈጥሮው የተነሳ እግዚአብሔርን አይፈልግም ። ወደ እግዚአብሔር ለመምጣት ምንም ፍላጎት የለውም ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርም ጠላት ነው ። የሰው ኃጢአት ሰውን ከእግዚአብሔር ለይቶ በገሃነም ውስጥ ለዘላለም እንደሚቀጣው አስቀድሞ እግዚአብሔር ገልጿል። መፍትሄ ከሌለ ይህ በእርግጥ መጥፎ ዜና ነው።

ወንጌል ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመሰቀል ላይ ባቀረበው መሥዋዕት የኃጢአታችንን ዋጋ ሊከፍል የመጣውን ለእኛ ምትክ የሆነውን የሚያብራራ ነው ። ክርስቶስ ንጉስ ካህን እና ነብይ በመሆን ከሰው ልጆች የሚጠበቀውን በሙሉ ፈፅሞ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር አስታርቋል ። ይህን ወንጌል በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያየ መንገድ ተገልፆ እናገኛለን ። ወንጌላትን በጥንቃቄ ብንመለከት ይህንን በሰፋት ያብራራሉ ።

አራቱም ፀሐፊዎች የተለያየ የአፃፃፍ ዘዴ ቢኖራቸውም ነገርግን አራቱም ኢየሱስ መሲሕ ፣ ሲጠበቅ የነበረው አዳኝ መሆኑን አረጋግጠዋል ።

ማቲዎስ ኢየሱስ የአይሁድ ንጉስ መሆኑን ሲተርክልን – ማርቆስ ደግሞ ኢየሱስ ታማኝ ንፁህ እና ትሁት አገልጋይ እንደሆነ ይገልፅልናል ። – ሉቃስ ፦ ኢየሱስ እንደ እኛ የተራበ ፣ የደከመ ፣ የተፈተነ ፍፁም ሰው እንደሆነ ሲተርክ – ዮሐንስ፦ እርሱ ከዘላለም የነበረ ፣ ፍጥረታትን የፈጠረ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ያስረዳናል ።

በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 1:14-15 መሰረት በማድረግ የወንጌል ሰብከት መልዕክትን ለመረዳት ጥረት እናድርግ ።

ይህ የማርቆስ ወንጌል ልዩ የሚያደርገው ከኢየሱስ ትምህርቱ የበለጠ የኢየሱስን ተግባር ስለሚያጎላ ነው። ከክርስቶስ ሕይወት ውስጥ ከአንዱ ክፍል ወደ ሌላው በፍጥነት እየተሸጋገረ በቀላሉ ጽፎታል።

እንደ ማቴዎስ የትውልድ ሐረግ አይጀምርም ምክንያቱም አሕዛብ ስለ እርሱ ዘር ጉዳያቸው አይደለም ። በገሊላ፣

በዙሪያው ባሉት አካባቢዎች እና ከዚያም ወደ ይሁዳ ያደረገውን ጉዞ ስንከተል የማርቆስ ዘገባ ምን ያህል ፈጣን አድርጎ እንዳሰቀመጠው እንገነዘባለን። ነገርግን አብዛኛውን ነገር በፍጥነት ቢያቀርብልንም የክርስቶስን ወንጌል በመግቢያው ከማብራራት ይጀምራል ።

ማርቆስ 1፡14-15 (አዲሱ መ.ት) ። [14] ዮሐንስ እስር ቤት ከገባ በኋላ፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ወንጌል እየሰበከ ወደ ገሊላ ሄዶ፣[15] "ጊዜው ደርሶአል፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች፤ ንስሓ ግቡ፤ በወንጌልም እመኑ" እያለ ይሰብክ ነበር ።

በእነዚህ ሁለቱ ቁጥሮች የወንጌል ሰብከትን መልዕክት በአራት  መንገድ ማርቆስ ይገልፅልናል ።

1, የእግዚአብሔር ተሰፋ መሆኑን ማወጅ። ማለትም ወንጌሉ መጤ ወይንም እንግዳ ነገር እንዳልሆነ እና የእግዚአብሔር የማድን ዕቅድ መሆኑን ማወጅ ።

2, የእግዚአብሔር መንግሰት አሁን በምድር ላይ መሆኑን ማወጅ ። ማለትም እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር በመሆን የሰውችን ልብ እና አስተሳሰብ በመለወጥ ሰዎችን መግዛት መጀመሩን ማብሰር ።

3, ንስሐ መግባት እንዳለባቸው ማወጅ ። ማለትም ቀድሞ የነበረውን የአመፅን አስተሳሰብ በመቀየር የሰላምን አስተሳሰብ መያዝ ።

4, ይህን መልካሙ ዜና ማመን እንዳለባቸው ማወጅ ። ማለትም በእግዚአብሔር እና በእግዚአብሔር ተሰፋዎች ማመን እና የመንግሥቱ የተሰፋ ቃል እዚህ እንዳለ ማመን ።

ማርቆስ በቁጥር 14 እና 15 ሐሳቡን ለመግለጽ የሚጠቀማቸውን ቃላት አያብራራቸውም ። ምክንያቱም በዘመኑ የነበሩ ሰዎች የቃላቱ ትርጉም ምን እንደሆኑ ስለሚያውቁ ሀሳቡ በቀላሉ ይገባቸዋል ።ስለዚህ ፀሀፊው ማርቆስ ያላብራራቸውን ቃላት በማብራራት ሀሳብን ለመረዳት ጥረት እናደርጋለን ።

– ቁጥር 14 የሚጀምረው የመጥምቁ ዮሐንስን መታሰር መግለጽ ከመጀመር ነው ። የዮሐንስ አገልግሎት መጠናቀቁን እና ኢየሱስ አገልግሎቱን መጀመሩን የሚያመለክት ነው ። ማርቆስ ይህንን መግለፅ የፈለገው ዮሐንስ መንገድ የመጥረግ ስራውን እንደጨረሰ እና ኢየሱስ በዚህ መንገድ እንደመጣ ለመግለጽ ነው ።ይህንን ቀጥሎ ባለው አረፍተ ነገር መመልከት እንችላለን ።መጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎቱን ጨረሰ - ኢየሱስ ደግሞ አገልግሎቱን ጀመረ።  ዮሐንስ ሊመጣ ያለው መሲሕ እንዲመጣ የመጣ እንጂ እርሱ እራሱ የሚመጣው መሲሕ አይደለም ። ይህንን መልዕክት ለማስተላለፍ ነው የዮሐንስን መታሰር ግልጽ አድርጎ የጀመረው ።

## – ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ወንጌል መሰበኩ ።

ኢየሱስ የሰበከው የምስራች የእግዚአብሔር ተልዕኮ ነው ።

በዚህ ምድር ላይ ብዙ የምስራቾች አሉ።ለምሳሌ ፦ ልጅ መወለዱ የመሰራች ነው ፣ ሰርግ ፣ ከበሽታ መፈወስ ፣ የኑሮ ውድነት መቀነስ ወዘተረፈ ። እነዚህን የምስራቾች ሰንሰማ እንደስታለን ። ይህ ብቻ ሳይሆን የህይወታችንንም አቅጣጫ ይቀይራሉ ። ይህ የምስራች ግን ለየት የሚያደርገው ከእግዚአብሔር ለሰው መሆኑ ነው ።

# ወንጌል ማለት ምን ማለት ነው ?

ወንጌል  የሚውለው ቃል εὐαγγέλιον ኢውኤንጌልዮን ከሚል የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን

ኢው ማለት Good ማለት ሲሆን    ኤንጌሊዮን ማለት ደግሞ Angel መልዕክተኛ ወይንም message ማለት ነው ። ሁለቱም ቃል አብረው ሲመጡ Good news ማለት ነው ። ይህ ቃል መልካም ነገር ለሆኑ ሁሉ የሚሰራ ነው ።    ነገርግን በስአቱ የነበረው ማህበረሰብ ፅሁፎች ውስጥ በሰፋት የሚገኘው ንጉስ ከሚያደርገው ድል ጋር የሚያያዝ ነው ። ቲም ኬለር እንደዚህ ይላል ፦ አንድ ንጉሥ ወራሪውን ጦር ካሸነፈ ፡ ጠላትን አሸንፋል እና መልዕክተኞችን ይልካል እነዚህም አብሳሪዎች በዚህ ድል ደስ ይበላችሁ እና በዚህ ድል ኑሩ ይላሉ ።

የዚህ የምስራች ትርጉምም በብሉይ ኪዳን ዘመንም የነበር ነው ። መንግስታት ጦርነት ሲገጥሙ  ጦርነቱ ከዝግጅቶ ጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ቀናት ሊፈጁ ይችላሉ። የጦር ግንባር ላይ ሄደው ነው የሚፋለሙት battle filled ። ሁለቱም መንግስታት ቅጥራቸውን ለቀው ፣ ህዝባቸውን ትተው ፣ ወታደሮቻቸውን አስከትለው ለውጊያ ወደ ጦር ግንባር ይሄዳሉ ። እንግዲህ ግንባር ላይ እየተካሄደ ያለውን ጦርነት እቤት የቀሩት የሁለቱም መንግስታት ሹማምንቶች እና ተራው ማህበረሰብ አያውቅም ። እንደዚህ ዘመን በቴክኖሎጂ  የታገዘ ዘመን አልነበረም ። ከዚህ የተነሳ የጦርነቱ ውጤት ምን እንደሆነ መጥቶ የሚነግራቸውን መልዕክተኛ ኮቴን ለመመልከት አይናቸውን ወደ ውጭ ወርውረው ኮቴውን ይጠባበቃሉ። በታላቅ ተሰፋ ይጠባበቃሉ ። ምክንያቱም የጦርነቱ ውጤት ድል መንሳትም ሆነ ድል መነሳትም እንደ ህዝብ ቀጣይ ሁኔታቸውን ይወሰናል ።

መንግስታቸው ከተሸነፈ ትርጉሙ ፦ ነገስታቶቻቸው አፈግፍገው ከተመለሱ ወይ ደግሞ ከሞቱ - ያሸነፈው የጠላት ሀገር ንጉስ ሰራዊቱን አስከትሎ ልጆቻቸውን ባርያ ያደርጋሉ ፣ ሴቶቻቸውን ይወስዳሉ ፣ ንብረቶቻቸውን ይዘርፋሉ ። ስለዚህ የጦርነቱ ግንባር ወሬ በከባዱ ያሳሰባቸዋል ። ከጦርነቱ መጠናቀቅ በኋላ የሚሰማው ዜና መቀጠል አለመቀጠላቸውን - መኖር አለመኖራቸውን የሚወስን ነው ። በጣም የሚገርመው ሰገነት ላይ ቆመው በጣም ከመጓጓታቸው የተነሳ የጦሩን ወሬ ፣ የጦሩን ወሎ ይዞ የሚመጣውን ሰው አሯሯጡን እያዩ ፣ እግር አጣጣሉን እያዩ ዜናውን ይገምታሉ ።  በጣም ከመቋመጣቸው የተነሳ እስኪደርስ እንኳን አይጠብቁትም ።

ይህንን ታሪክ በደንብ ለመረዳት 2ኛ  ሳሙ 18:19... መመልከት ይረዳናል ።

2ኛ ሳሙኤል 18 ፡19-27 (አዲሱ መ.ት) ።

19 በዚህ ጊዜ የሳዶቅ ልጅ አኪማአስ፣ “እግዚአብሔር ጠላቶቹን የተበቀለለት መሆኑን ሮጬ ሄጄ ለንጉሡ
የምሥራች ልንገረው” አለ። 20 ኢዮአብም፣ “ዛሬ የምሥራቹን ወሬ የምትወስድለት አንተ አይደለህም፤ የንጉሡ
ልጅ ስለ ሞተ፣ ዛሬ ሳይሆን፣ የምሥራቹን ሌላ ጊዜ ታደርስለታለህ” አለው። 21 ከዚያም ኢዮአብ ለኢትዮጵያዊው፣
“ሂድና ያየኸውን ለንጉሡ ንገር” አለው፤ ኢትዮጵያዊውም ኢዮአብን እጅ ነሥቶ እየሮጠ ሄደ። 22 የሳዶቅ ልጅ
አኪማአስም እንደ ገና ኢዮአብን፣ “የመጣው ይምጣ፤ እባክህ ኢትዮጵያዊውን ተከትየው ልሩጥ” አለው።
ኢዮአብ ግን፣ “ልጄ ሆይ፣ መሄድ ለምን አስፈለገህ? ሽልማት የሚያስጥህ ምን የምሥራች ይዘህ ነው?” ብሎ
መለሰለት። 23 አኪማአስም፣ “የመጣው ይምጣ፤ መሄድ እፈልጋ ለሁ” አለ። ስለዚህም ኢዮአብ፣ “እንግዲያውማ
ሩጥ!” አለው። ከዚያም አኪማአስ በሜዳው መንገድ ሮጦ ኢትዮጵያዊውን ቀድሞት ሄደ። 24 ዳዊት
በውስጠኛውና በውጭኛው በሮች መካከል ተቀምጦ ሳለ፣ ጠባቂው ቅጥሩ ላይ ወዳለው ወደ በሩ ሰገነት ጣራ
ወጥቶ ወደ ውጭ ሲመለከት አንድ ሰው ብቻውን ሲሮጥ አየ። 25 ጠባቂውም ተጣራና ይህንኑ ለንጉሡ ነገረው፤
ንጉሡም፣ “ብቻውን ከሆነ መልካም ወሬ ይዞ የመጣ መሆን አለበት” አለ። ሰውየውም እየቀረበ መጣ።

[26] ከዚያም ጠባቂው ሌላ ሰው ሲሮጥ አይቶ፣ ዘበኛውን ተጣራና፣ “እነሆ ሌላም ሰው ብቻውን እየሮጠ በመምጣት ላይ ነው!” አለ። ንጉሡም፣ “ይኸኛውም መልካም ወሬ ይዞ የመጣ መሆን አለበት” አለ። [27] ጠባቂውም፣ “የመጀመሪያው ሰው ሩጫ የሳዶቅን ልጅ የአኪማአስን ሩጫ ይመስለኛል” አለ። ንጉሡም፣ “እርሱማ ጥሩ ሰው ነው፤ የምሥራች ሳይዝ አይመጣም” አለ።

የወንጌል ትርጉምን በዚህ አውድ ለሚያውቁ ሸዎች ኢየሱስ ወንጌልን ይሰብካል ። በሰብከቱ ውስጥ እጅግ ወሳኝ አራት ነጥቦችን እናገኛለን ።

**– ጊዜው ደርሷል ፦** እዚህ ላይ ጊዜው የሚለው ቃል፦ ተራ የጊዜን መቁጠሪያን እያወራ አይደለም ። ስለእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ የሚያወራው ነው ።በዚህ ምንባብ ማርቆስ የወንጌልን ቀዳሚነት አጽንዖት ሰጥቷል– የወንጌል መልእክት ታሪካዊ እውነታዎችን ይዟል። ይህ ቃል አስቀድሞ ተሰፋ የተሰጠ መሆኑን የሚያሳይ ነው ። ይህን አይነት አገላለጽ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሰፋት ተገልፆ እናገኛለን ። ለምሳሌ ፦

ሮሜ 5:6 “ገና ደካሞች ሳለን፣ ልክ ጊዜው ሲደርስ፣ ክርስቶስ ስለ ኀጢአተኞች ሞቶአልና።”

ገላ 4:4 ። “ነገር ግን የተወሰነው ዘመን በደረሰ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን፣ ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፤”

**ተሰፋው ምንድነው ?** አህዛቡ ማህበረሰብ ተሰፋ የሚያደርግ ማህበረሰብ አይደለም ። ጳውሎስ በኤፌሲዮን መፅሐፉ እንደሚነግረን “በዚያን ዘመን ከክርስቶስ ተለይታችሁ፣ ከእስራኤል ወገንነት ርቃችሁ፣ ለኪዳኑም ተሰፋ ባዕዳን ሆናችሁ፣ በዓለም ላይ ያለ ተስፋና ያለ እግዚአብሔር እንደ ነበራችሁ አስታውሱ።” — ኤፌሶን 2፥12 (አዲሱ መ.ት) ። ይህ ተሰፋ የእስራኤል ተሰፋ ብቻ ነው ። የእስራኤል ህዝብስ የሚጠብቀው ተሰፋ ምንድነው ?

1, እስራኤላውያን በምድር ሳሉ እራሱ እግዚአብሔር እንደሚመጣ ፣ እርሱ እግዚአብሔር መጥቶ እንደሚያድናቸው ፣ በመካከላቸው እንደሚያድር እና ክብሩን እንደሚመልስ ተሰፋ ያደርጉ ነበር ።

2, በሁለተኛው ቤተመቅደስ በሚባለው ዘመን ደግሞ፦ መሲሑ ይመጣል ፣ የመጨረሻው ዘመን አዳኝ ይገለጣል ፣ እኛንም ነፃ ያወጣናል ጠላቶቻችን ላይ ይፈርዳል የሚል አመለካከት ነበራቸው ።

ስለዚህ ይህ መፈፀሙ ለእነርሱ የምሰራች ነበር። እግዚአብሔር በህዝቡ መካከል መሆኑ ለእስራኤል ትልቅ ደሰታ እና ተሰፋ መሆኑን በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንመለከታለን ።

**– ኢሳ 12:6 - “የጽዮን ሕዝብ ሆይ፤ እልል በሉ፤ በደስታም ዘምሩ፤ በመካከላችሁ ያለው የእስራኤል ቅዱስ ታላቅ ነውና።”**

**– (ዘካ 2:10 ““የጽዮን ልጅ ሆይ፤ እልል በዪ፤ ደስም ይበልሽ፤ እኔ እመጣለሁና፤ በመካከልሽም እኖራለሁ” ይላል እግዚአብሔር።”**

**በመካል መኖር የመቅደስ አገላለጽ ነው ። ዘፀ 25:8 ። ““ከዚያም መቅደስ እንዲሠሩልኝ አድርግ፤ እኔም በመካከላቸው እድራለሁ።”**

ለእስራኤልያዊያ እግዚአብሔር በመካከላቸው መኖሩ ትልቅ ተሰፋ እና የምሰራች መሆኑን በዚሁ በማርቆስ

መፅሐፍ መጀመርያ ላይ እናገኛለን ። ማርቆስ 1:2-3 (አዲሱ መ.ት) ² በነቢዩ በኢሳይያስ፣ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፤ “እነሆ መንገድህን የሚያዘጋጅ መልእክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ፤ ³ ‘የጌታን መንገድ አዘጋጁ፤ ጥርጊያውንም አስተካክሉ እያለ በበረሓ የሚጮኽ ድምፅ’።”

በእነዚህ ቁጥሮች የምናገኘው ፦ ዮሐንስን መንገዱን የሚጠርግለት እግዚአብሔር መሆኑን ነው ። ይህንንም ከኢሳያስ 40 የተወሰደ ነው ። በኢሳያስ መፅሐፍ እንደምንመለከተው ፦

1ኛ, **እግዚአብሔር እራሱ እንደሚመጣ** ቁጥር 3 እና 9 ። ቁጥር 3 “የዐዋጅ ነጋሪ ድምፅ እንዲህ ይላል፤ “የእግዚአብሔርን መንገድ፣ በምድረ በዳ አዘጋጁ፤ ለአምላካችን አውራ ጐዳና፣ በበረሓ አስተካክሉ።”

ቁጥር 9 “አንተ ለጽዮን የምሥራችን የምትነግር፤ ከፍ ወዳለው ተራራ ውጣ፤ አንተ ለኢየሩሳሌም ብሥራት የምትነግር፣ ድምፅህን ከፍ አድርገህ ጮኽ። ከፍ አድርገው፤ አትፍራ፤ ለይሁዳም ከተሞች፣ “እነሆ፤ አምላካችሁ!” በል።”

2ኛ, **ክብሩን እንደሚገልጥ**፦ ቁጥር 5 “የእግዚአብሔርም ክብር ይገለጣል፤ ሰው ሁሉ በአንድነት ያየዋል፤ የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሮአልና።”” ስለዚህ ሲጠበቅ የነበረው እግዚአብሔር በመካከላቸው መገኘቱ ነው ብሰራቱ ( የምሰራቹ) ።

# – የእግዚአብሔር መንግሰት መቅረብ !

የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች፦ የእግዚአብሔር መንግሥት ጽንሰ-ሐሳብ በተለያዩ የቅዱሳት መጻሕፍት ምንባቦች ውስጥ የተለያዩ የትርጓሜ ጥላዎችን ይይዛል። በሰፊው ሰንናገር፣ የእግዚአብሔር መንግሥት በአጽናፈ ዓለም ሁሉ ላይ የዘላለም ሉዓላዊ አምላክ አገዛዝ ነው። ብዙ የቅዱሳት መጻሕፍት ምንባቦች እንደሚያሳዩት እግዚአብሔር የማይካድ የፍጥረት ሁሉ ንጉሠ ነገሥት ነው፡ "እግዚአብሔር ዙፋኑን በሰማይ አጸና፥ መንግሥቱም ሁሉን ትገዛለች" ( መዝ. 103፡19 )። እና፣ ንጉስ ናቡከደነፆር እንዳወጀ፣ "መንግስቱ የዘላለም መንግሰት ነው" ( ዳንኤል 4፡3 )። ያለው ሰልጣን ሁሉ በእግዚአብሔር የተቋቋመ ነው ( ሮሜ 13፡1 )። ሰለዚህ፣ በአንድ በኩል፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ያለውን ሁሉ ያጠቃልላል።

በጠባቡ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት በፈቃዳቸው ለእግዚአብሔር ሥልጣን በሚገዙ ሰዎች ልብ እና ሕይወት ላይ የምትገዛ መንፈሳዊ አገዛዝ ነው። እግዚአብሔርን ሥልጣን የሚቃወሙ እና ለእርሱ ለመገዛት ፈቃደኛ ያልሆኑ የእግዚአብሔር መንግሥት አካል አይደሉም። በአንጻሩ የክርሰቶሰን ጌትነት የተቀበሉ እና በልባቸው ለእግዚአብሔር አገዛዝ በደሰታ የተገዙ የእግዚአብሔር መንግሥት አካል ናቸው።

ከዚህ አንጻር፣ የእግዚአብሔር መንግሥት መንፈሳዊ ነው - ኢየሱሰ መንግሥቱ ከዚህ ዓለም እንዳልሆነ ተናግሯል ( ዮሐንስ 18፡36 )፣ እና የእግዚአብሔር መንግሥት አካል ለመሆን ንስሐ መግባት እንደሚያሰፈልግ ሰበከ ። የእግዚአብሔር መንግሥት ከደኅንነት ጋር ሊመሳሰል እንደሚችል ግልጥ ነው ማር 10:17-27። በዚህ የማርቆስ 10 ምንባብ ውሰጥ የእግዚአብሔር መንግሰት ከ Salivation ጋር የተያያዘ ነው ።ይህንንም ከባለጠጋው ጥያቄ ፣ ከኢየሱሰ መልሰ እና ከደቀመዛሙርቱ ጥያቄ እንረዳለን ።

1, ቁጥር 17 “ከዚያ ተነሥቶ መንገዱን ሲጀመር፣ አንድ ሰው ወደ እርሱ እየሮጠ መጣ፤ በፊቱም በጒልበቱ ተንበርክኮ፣ “ቸር መምህር ሆይ፤ **የዘላለምን ሕይወት ለመውረሰ ምን ማድረግ ይገባኛል”** አለው።” –የዚህ ሰው ጥያቄ የዘላለምን ህይወት መሰረሰ ነው ።

2, ቁጥር 23 "ኢየሱስ ዙሪያውን በመመልከት ደቀ መዛሙርቱን፣ "ለሀብታሞች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት እንዴት ከባድ ነገር ነው!" አላቸው።" –ኢየሱስ ወደእግዚአብሔር መንግስት መግባት እንደማይችል ገለፀ ።

3, ቁጥር 26 "ደቀ መዛሙርቱም ይበልጥ በመገረም፣ "ታዲያ ማን ሊድን ይችላል?" ተባባሉ።" – በዚህ መስፈርት ማን ሊድን ይችላል አሉ ።

– በእነዚህ ወስጥ በዋናነት የምናየው የእግዚአብሔር መንግስት ድነት እና የዘለአለም ህይወት መሆኑን ነው የምናየው ።

## – ንሰሐ ግቡ!

ንሰሐ ምንድነው ? መፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ ንሰሐ የሚለው ቃል በቀጥታ ሲተረጎም በግሪኩ to change mind አዕምሮን መቀየር ፣ አስተሳሰብን መለወጥ ። በዕብራይስጡ to the ground የሆነ ቃል ነው ። የቃሉም ትርጉም turning around. በቀጥታ መዞር ፣ መንገድ መቀየር ነው ። ወደ ምስራቅ ከነበርንበት ወደ ምዕራብ 180 ዲግሪ መዞር ነው ። ለእግዚአብሔር ጀርባ ሰጥተን ከነበረ ወደ ፊቱ 180 ዲግሪ መዞር ነው ። እውነተኛ የመፅሐፍ ቅዱስ ንሰሐ ከመፀፀት ወይንም ከመከፋት በላይ ነው ።in fact this is part of repentance. Repentance is not emotion. Repentance is decision.

አዲስ ኪዳን ላይ ሜታኖኦ የሚለውን ቃል ይጠቀማል ። ሜታኖኦ ማለት ከእውቀት በኋላ የተገኘ ሆኖ አዕምሮን እና አላማን መለወጥ ማለት ነው ። ንሰሐ ያለፈን ስህተት እንደሆነ ማወቅ እና ወደፊት በትክክል ለማሰብ መወሰንን ያካትታል ። ንሰሐ የገባ ሰው ቀደም ሲል ስለተቀበለው አስተሳሰብ ሁለተኛ (ተለዋጭ ) ሀሳብ አለው ። ስለ እግዚአብሔር ፣ ስለ ሀጥያት ፣ ስለ ቅድስና እና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ የአመለካከት ለውጥ ፣ አዲስ የአስተሳሰብ መንገድ አለው ።

በአጭሩ ንሰሐን ለመረዳት ኃጢአትን መረዳት ወሳኝ ነው ። ነገርግን ንሰሐ የሚገቡት ስለየትኛው ኃጢአታቸው ነው ?

በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኃጢአያት በተለያዩ መንገዶች ተፅፈው እናገኛለን ።

1. ሐማርቲያ፦ (ሀጥያት)። ፣ ሐማርቶሎስ፦ ደግሞ ሀጥያተኛ ። ፣ እና ሀማርተነው፦ ደግሞ ሀጥያትን ማድረግ ነው ። እነዚህ ቃላት የሚያሳዩት ወደታቀደለት አለማ አለመድረሰን ነው ። አንድ ቀስተኛ በተዘጋጀለት ሰርክል ውሰጥ ያለችው ነጥብ ላይ ካልሰካ ሐማርቲያ ይባላል ። ሳተ ወይንም ግቡን አልመታም እንደማለት ነው ።

2ኛ, አድኪያ ፦ ይህ አመፅ የሚለውን የሚያመለክት ቃል ነው ። እግዚአብሔር ለሰው ልጅ መስፈርት ሰጥቶ የሰው ልጅ ከእዚህ መለኪያ ጋር አለመሰማማቱን የሚያሳይ ነው ።

3ኛ, ታራፕቶማ ፦ ይህ ደግሞ መተላለፍን የሚያመለክት ነው ። ይህም ሰው እግዚአብሔር ከሰጠው መንገድ ለቅቆ በሌላ መንገድ መራመዱን የሚያሳይ ነው ።

4ኛ, አኖሚያ ፦ (አመፅ) ማለት ነው ። ይህም ያለ ህግ ወይንም ከህግ ውጪ መኖርን የሚያመለክት ነው ።

5ኛ, ኦፋይሊቲስ ፦ (እዳ ያለበት) ማለት ነው ።

እኔ እንደሚመስለኝ ጉዳዩ ከመንግስት ስለተያያዘ አኖሚያ የሚለው ይመስለኛል ። ማለትም አመፅ ነው ።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዓመፅ ምን ይላል?

ህግ አልባ መሆን ከህግ ጋር መቃረን ወይም ህግን ሳታከብር መንቀሳቀስ ማለት ነው።

ኃጢአት ገዳይ በሽታ ነው ፣ ነፍስህን እስኪበላው ድረስ አይለቅም። ኃጢአት ራሱ ገሃነም ነው ፣ እግዚአብሔርን ያዋርዳል ፣ እግዚአብሔርን ያስቆጣ ። ኃጢአት እንዳናደርግ የተከለከልነው በጥሩ ምክንያቶች ነው። ስለዚህ በኃጢያአታችን እንጸጸት። ምክንያቱም ኃጢአትን ስንሠራ የእግዚአብሔርን ሕግ እየጣስን ፍቅሩንና ምሕረቱን እየተሳደብን ነው ። ኃጢያትን መስራት - እንዲሁ ተራ ፍራት ብቻ እና እራስን የማቅለል ስሜት ብቻ አይደለም። ነገር ግን ኃጢአት መሥራት ያድነን ዘንድ አንድ ልጁን በቸርነቱ የሰጠንን አፍቃሪ አምላክን ማሳዘን ነው ። ብዙ ውለታ ያደረገልንን እረኛችንን እናሳዝናለን። በጥልቀት በልባችን ያደረግነውን እንጸየፍ እና እንጸጸት። የሠራነውንም ኃጢአት ለትሑታን አምላክ እንናናዘዝ።

መንገዳችንንም ከጥፋት መንገድ ወደ እግዚአብሔር በማዞር ቅንነታችንን እናሳይ። በእርሱ እንድንኖር እራሳችንን ከኃጢአት እናፋታ ፣ እና ንስሀ ለመግባት ወደ ኋላ አንበል። ክርስቶስ ያልሞተለት ኃጢአት የለም። ስዎቸ ለዓለም ጀርባቸውን ሰጥተው ወደ እርሱ ከተመለሱ ክፋዎችን ለመቀበል እጁ ሁል ጊዜ ክፍት ነው። የንሰሐ አባትና ወዳጅ ነው። ኃጢአታችን በጣም ከባድ ቢሆንም - ይቅርታ የማይደረግልን ግን ንሰሐ አለመግባታችን ነው። ንሰሐም ባለመግባት ሌላ ከባድ ኃጢአት አንጨምር። ወደ ክርስቶስ እንሂድ ወደ ደሙ እንጠጋ ፣ እርሱም ኃጢአታችንን ያነጻል። ከመንፈስ ብርታት ለማግኘት እንጸልይ እና በቅዱስ ቃሉ ራሳችንን እናጽናና።

**– ማመን** - ይህ ማለት በእግዚአብሔር እና በእግዚአብሔር ተስፋዎች እናምናለን ማለት ነው። የመንግሥቱ የተሰፋ ቃል እዚህ እንዳለ እናምናለን እናም የእግዚአብሔርን ጸጋ በሚሰጠን ንጉሥ በኢየሱስ እናምናለን - ከሰይጣን ነፃ መውጣት ፣ ይቅርታ እና ከእግዚአብሔር ጋር አዲስ ግንኙነት እና አዲስ ሕይወት ፣ ይህም የተሰፋውን የተሰፋ ቃል የሚያጠቃልለው እና በትንሳኤአችን የሚጠናቀቅ ነው ።

እነዚህ ሁለቱ ቁጥሮች በሰፋት በቀጣዩ ምዕራፎች ይቀጥላሉ ።

የእግዚአብሔር የምስራች በክርስቶስ የተሰራ ለሚያምኑ ሁሉ የሚሆን የድነት ስራ ነው ። ይህ የምስራች ፦ አምላክ ሰው የሆነበት ፣ በሰዎች የተተፋበት ፣ እርቃኑን የተሰቀለ ፣ ጎኑን በጦር የተወጋ ፣ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የተዋረደ ፣ የኃጢአትን እዳ የከፈለ ፣ ሰዎችን በጻድቁ እግዚአብሔር ፊት ያቆመ ፣ የዘለአለም ዋስትና የሚሰጥ ታላቅ ዜና ነው ።የዘለአለም ህይወት ብቸኛው መንገድ ፣ የክርስትና መሰረት ፣ የፍጥረት መታደስ ተሰፋ – የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ስራ ነው ። ከዚህ በተቃራኒ ፣ የተሻሻለ እና የተሻሻለ ወንጌል የሚሰብክ ሁሉ የተረገመ ይሁን ! ይላል ጳውሎስ ።

**ይቀጥላል** ..